# በደስታ ብዛት ያገኘውን ብር መጥራት ያቃተው ዕድለኛ

"በምን ሎተሪ ዕድለኛ ሆነህ ነው የመጣህው"

"በልዩ ሎተሪ አንደኛ ዕጣ ነጠላ ቲኬት ደርሶኝ"

"ምን ያህል ነው የደረሰህ"

"ሰባት መቶ ሃምሳ ብር፣ሰባት ሺ አምሰት መቶ ብር ..."ሲል መለሰ ፡፡ጠያቂው የብር መጠኑ ትክክል እንደልሆነ ያውቃል፡፡

"ረጋ በልህ መልስልኝ ስንት ነው የደረሰህ"

አሁንም ድንጋጤ ሳይለቀው"ሰባት ሺ አምሰት መቶ "አለ

ጠያቂው አሁንም ረጋ ብሎ እንዲመለስ ነገረው፡፡በድምጽ መቅረጫ እየቀረጸ በመሆኑ መረጃውን ይፈልጋዋል፡፡

አሁንም የተሳሰተ መልስ ሰጠ"ሰባ አምስት ሺ"

አሁን ምን ያህል እንደደረሰው መንገር የግድ እንደሆነ ጠያቂው ተገነዘበ፡፡ የደረሰውን ብር ነገረው ጠያቂው ፡፡



እሱም በስንት መከራ "ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ ብር "የሚለውን ተነፈሰ፡፡ ደስታው እንደዚህ የተለያየ ምለሽ እንዲሰጥ አድርጎታል አይነ አፋሩ አየነው ደስታ ብቻ ሳይሆን ያሰለፈው ሕይወት መባቻ ላይ መድረሱ አሰደንግጦታል፤ ሚያዝያ 30 በወጣው የልዩ ሎተሪ ነጠላ ቲኬት

ሰሜን ማዘጋጃ አካባቢ ዓባይ ግሮሰሪ በብርጭቆ አጣቢነት ነው የሚሰራው፡፡አንድ ዓመት ሙሉ ትምህርቱን አቋርጦ ተቀምጧል፡፡ ቀጨኔ ከሚኖረው ወንድሙ ጋር ለመኖር ከምስራቅ ጎጃም አዲስ አበባ ግንቦት 2002 ይመጣል፡፡

ያገኘው ስራ ብርጭቆ ማጠብ ነበር፡፡ አልተግደረደረም ስራውን ጀመረ፡፡ምስራቅ ጎጃም አነደድ ወረዳ የሚገኙት ቤተሰቡቹ ችግረኛ በመሆናቸው ነበር ትምህርቱን ለማቋረጥ የተገደደው፡፡ አራት ወንድምና አራት እህቶች አሉት፡፡ ስለ ግሮሰሪው ስራ ሲናገር

“ግሮሰሪ ውስጥ ቀኑን ሙሉ ነበር የምሰራው፡፡ እንደውም እዚያ ነው የምውለው የማድረው ማለት ይቻለል፡፡ አሁን ከብርጭቆ ማጠብ ወደ ማስተናገዱ ስራ ልዛወር በምልበት ወቅት ነው የደረሰኝ፡፡” ብሏል

“ለምን ሙሉ ሎተሪ አልገዛህም” ተብሎ ሲጠየቅ “ግማሹን ነበር ያገኘሁት” በማለት አጋጣሚውንም እንዲህ ያስታውሳል “ሎተሪ የተመለከትኩት (ሰባት ሰዓት አካባቢ ነበር) ዕድለኛ መሆኔን ያወኩት፡፡ ማታ ለወንድሜም ነገርኩት” በደረሰው ገንዘብ ምን ለማድረግ እንዲህ ሲል ተናግሯል “ቤተሰቦቼን ለመጦርና በንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት እፈልጋለሁ”